# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 94 የካቲት 25 2002 ዓ.ም


ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።

ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!

## ወያኔ በ1977ቱ ረሃብ ለትግራይ ተጎጂዎች የተለገሰውን በርካታ ሚሊዮን ዶላር የጦር መሳሪያ ሲገዛበት እንደነበረ ቢቢሲ አገለጠ

በ1977 ዓም በትግራይ በተከሰተው ከፍተኛ ረሀብ የተጎዱ ወገኖችን ለመታደግ ከበርካታ ምእራባዊያን ለጋሽ ሃገራት ተለግሶ የነበረውን በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ወያኔ ለጦር መሳሪያ ግዢ ማዋሉን ለማረጋገጥ እንደቻለ በዓለማቹን ታዋቂ የሆነው ቢቢሲ በትናንትናው ዕለት ባሰራጨው ዜና ገለጸ። የአፍሪካ ቀንድ ኤክስፐርት የሆነው የቢቢሲው ጋዜጠኛ ማርቲን ፕላውት በዘገባው ላይ እንደገለጸው ቀደም ብሎ እንደፈረንጆች አቆጣጠር ከ1984 እስከ 1985 ባለው ጊዜ ወያኔ በርሃብ የተጎዱ የትግራይ ዜጎቻችን ህይወት ለመታደግ ከበርካታ ሃገራት የተለገሰውንና እንደ ቦብ ጊልዶፍ አይነት ታዋቂ ግለሰቦች በዘመቻ አሰባስበው የለገሱትን በብዙ መቶ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ ለጦር መሳሪያ ግዢ ማዋሉን አረጋግጧል። የቀድሞ የህወሃት አመራር አባላት የነበሩትን አቶ ገብረ መድህን አራያንና ዶ/ር አረጋዊ በርሄን በመጥቀስ ዘገባውን ያወጣው ቢቢሲ ፣ በ እርዳታ ሥም በህወሃት እጅ ከገባው ገንዘብ ውስጥ 95 በመቶ ያህሉ ድርጅቱን ለማጠናከርና ለመሣሪያ ግዥ እንደዋለ የተቀረው 5 በመቶው ብቻ ረሃብተኛው ዘንድ እንደደረሰ ማረጋገጡን ገልጾአል። መለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረአበሮቹ እንዳሻቸው የሚመዘውሩት ህወሃት በትግራይ ህዝብ ላይ የፈጸመውን ወንጀል ቀደም ብለው ባገኙት አጋጣሚዎች ሁሉ ሲያጋልጡ የኖሩት ሃቀኛው ዜጋ አቶ ገብረመድህን አራያ ለቢቢስ በሰጡት የምስክርነት ቃል፤ ከአካባቢው እህል ገዝተው ለረሃብተኛው እንዲከፋፈል ለሚፈልጉ ለጋሽ ድርጅቶች እራሳቸው የእህል ነጋዴ መስለው እንዲቀርቡ እንደተደረጉና ከኋላው በአሸዋ የተሞሉ ብዙ ሺ ጆንያዎች የተደረደሩበትን ነገር ግን ለእይታ ያህል ብቻ ከፊት ለፊቱ እህል የያዙ በመቶ የሚቆጠሩ ጆንያዎች በማሳየት በርካታ ገንዘብ ይቀበሉ እንደነበር ገንዘቡንም ወዲያውኑ ለመለስ ዜናዊና ሌሎች ታማኝ ባለሟሎቹ ያስረክቡ እንደነበረ መናገራቸውን ዘግቧል። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## የወያኔው አገዛዝ በተቀናቃኞቹ ላይ ግድያ መፈጸሙን ኒውዮርክ ታይምስ ዘገበ

የወያኔው አገዛዝ ፍትሃዊና የተዋጣለት ምርጫ ለማድረግ ሁሉንም ዝግጂት ጨርሻለሁ እያለ ምእራባዊያንን በማጃጃል ላይ ባለበት ባሁኑ ወቅት በከተኛ ሁኔታ ሊቀናቀኑኝ ይቺላሉ በማለት የፈራቸውን የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት መግደል መጀመሩ ተዘገበ። በአሜሪካን ሃገር የሚታተመው ኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ከትናንት በስቲያ ማርች 2 ቀን ባወጣው ጽሁፉ ለፓርላማ ተመራጩነት የመድረክ ፓርቲ ካዘጋጃቸው አባሎቹ ውስጥ አንደኛው በታጣቂዎች የተገደሉበት መሆኑን የአረና ፓርቲ መሪ ገብሩ አስራትን በመጠቀስ ዘግቧል። በሌላም በኩል የቪኦኤውን ዘጋቢ ፒተር ሃይላይንን ጨምሮ በተለያዩ የዜና አውታሮች በስፋት በተዘገበው በዚህ ዜና እንደተገለጸው፣ ወያኔ እነኚህን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከማስፈራራትና ማስጠንቀቅያ ከመስጠት አልፎ የመድረክ የፖለቲካ ጥምር ፓርቲ አባል የሆኑትንና በሽሬ **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## መለስ ዜናዊ በወ/ት ብርቱካን ጉዳይ ከምርጫ በፊት አታናግሩኝ ማለቱ ታወቀ

የመድረክ አባል የሆኑት የቀድሞው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በአዲስ ከተማ ክፍለከተማ ተሰብስቦ ለነበረው ደጋፊያቸው እንደተናገሩት ወ/ት ብርቱካንን ለማስፈታት ጥረት የጀመረው የሽማግሌዎች ቡድን፣ ወደ መለስ ዜናዊ በሄደበት ጊዜ ከምርጫው በፊት በእርሷ ጉዳይ ላይ አታነጋግሩኝ የሚል መልስ አግኝቷል። ሽማግሌዎችም ምርጫው እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ የወ/ት ብርቱካንን ጉዳይ ላለማንሳት በመወሰን ዝምታን መርጠዋል።

መለስ ዜናዊ ወ/ት ብርቱካንን ያሰረበት ዋና ምክንያት በምርጫው ያለምንም ጠንካራ ተፎካካሪ ለመቅረብ አስቦ መሆኑን ብዙ ዎች በተደጋጋሚ ሲናገሩት እንደነበር የሚታወስ ሲሆን፣ አሁን አምባገነኑና ዘረኛው መለስ የሰጠው መልስ እስካሁን ድረስ ሲቀርቡ የነበሩትን አስተያየቶች እውነትነት የሚያረጋግጥ ነው።

መለስ ዜናዊ ከግንቦት97 ምርጫ በወሰደው ትምህርት ለስልጣኔ ያሰጉኛል ብሎ የጠረጠራቸውን ሰዎች በተለያዩ ወንጀሎች በመክሰስ **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## ወያኔ ለሚቀጥሉት 15 አመታት ያለምንም ተቃናቃኝ በስልጣን ላይ ለመቆየት እንደሚችል እየዛተ ነው

የካቲት 27 ቀን 2002 ዓም በወያኔና በተቃዋሚዎች መካከል "ዲሞክራሲ ምርጫና መድብለ ፓርቲ በኢትዮጵያ" በሚል ርእስ በቅርብ ጊዜ የሚካሄደውን የይስሙላ ምርጫ አስመልክቶ በተደረገ ክርክር የቀድሞው የስልጤ ነጻ አውጭ መሪ የአሁኑ የኢህአዴግ ህዝብ ግንኙነት ሃላፊ የሆነው ሬድዋን ሁሴን፣ "ለሚቀጥሉት 15 ዓመታት አገሪቱን የመምራት አቅምና ቺሎታ ያለው ተቃዋሚ ፓርቲ ስለማይኖር አመራሩን ኢህአዴግ እንደያዘ ይቀጥላል" በማለት ተናግሯል። በተመሳሳይ መልኩ የመለስ አማካሪ ሆኖ በማገልገል ላይ ያለው ሃይለማሪያም ደሳለኝ ወያኔ ኢትዮጵያን ከ15 ዓመታት በላይ የመግዛት ዕቅድ እንዳለው ሲያረጋግጥ የጃፓን ገዢ ፓርቲን እንደምሳሌ በመውሰድ ሊበራል ፓርቲ ጃፓንን ለ40 ዓመታት መምራቱን ወያኔም ከዚህ ጊዜ በላይ በመግዛት ሪከርዱን እንደሚይዝና ለዚህም ዋናው ምክኒያት አገዛዙ ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ በመሆኑ ነገር ግን ተቃዋሚዎች ዲሞክራሲን የማስፋፋት አቅም ስለሌላቸው ነው ሲል የወያኔን ህልም ይፋ አድርጎአል።

ጉዳዩን አስመልክቶ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንዳንድ ግለሰቦች " ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ መንግስት የሰብአዊ ዲሞክራሲያዊና መሰረታዊ የዜግነት መብቶቹን የሚያስፋፋና የሚያሳደግ እንጂ የሚያፍን የሚገድልና ዜጎች በማንኛውም አካባቢ ተንቀሳቅሰው የመስራት መብታቸውን የሚገድብ አይደለም" በማለት ሲገልጹ ፣የወያኔው አገዛዝ ግን ወደ ስልጣን ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ጸረ ዲሞክራሲና ጸረ ነጻነት ባህሪ የተጠናወተው ቡድን በመሆኑ ላንድቀን በስልጣን ላይ ውሎ ለማደር የሚያስችል የሞራል ብቃቱ የለውም ብለዋል። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## የፋሽስቱ ወያኔ መስራች ስብሃት ነጋ ህግ የሚጥሱትን ማሰር ፤ በጥይት ወይም በገዳይ መርፌ መግደል ተገቢ ነው ሲል መናገሩ ተዘገበ

በወ/ት ብርቱካን ላይ እየደረሰ ያለውን የግፍ እስር አስመልክቶ የቀድሞው የህወሀት መስራች እና መሪ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ የሰላምና ትብብር የሚባለው ተቋም ዳይሬክትር የሆነው ስብሀት ነጋ አጃንስ ፍራስ ፕሬስ ለተባለው ታዋቂ የዜና ድርጅት በሰጠው ቃለምልልስ "ህግ የሚጥሱ ካሉ ሊታሰሩ ፤በጥይት ተደብድበው ወይም በገዳይ መርፌ ተወግተው ሊገደሉ እንደሚችሉ መናገሩን የዜና ተቋሙ ይፋ ባደረገው ዘገባው ገልጾአል።

ወ/ት ብርቱካን መታሰራቸው ትክክል ነው፣ ከምርጫው በሁዋላ ከ 200 በላይ ንጹህ ኢትዮጵያውያን ለመግደል የተወሰደውም እርምጃ ትክክል ነው ያለው ስብሀት፣ ገዢው ፓርቲ ተመሳሳይ የሆኑ ችግሮች ካጋጠሙትም በእርምጃው እንደሚቀጥል ሳይሸሽግ ተናገርዋል።

የምአራብ ዲፕሎማቶች ወያኔ ምርጫውን ነጻ ለማድረግ የሚሞክረው እንደሚያሸንፍ እርግጠኛ ሲሆን ብቻ ነው ያለ ሲሆን፣ አሁን በአገሪቱ ውስጥ የሚታው ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ እንደሆነባቸውም መናገሩን ድርጅቱ ገልጿል።

የአቦይ ስብሀት ንግግርም ወያኔ አደጋ ውስጥ ከገባ ማንኛውንም የሀይል እርምጃ ከመውሰድ እንደማይቆጠብ የሚያመልክት ነው ተብሎአል።

## የወያኔ ካድሬ መምህራን ሳይቀሩ የትምህርት ፖሊሲውን እየተቃወሙት ነው ተባለ

የአገሪቱን የትምህርት እድገት ከጥራት ጋር አምጥቻለሁ እያለ የሚመጻደቀው ወያኔ፣ ከየካቲት 8 እስከ የካቲት 12 ቀን 2002 ዓም በደብረማርቆስ ከተማ በተደረገ የ6 ወራት የወያኔ ካድሬዎች የስራ ግምገማ ስብሰባ ውግዘት የደረሰበት መሆኑ ታወቀ።

በዚሁ ስብሰባ ላይ የአገዛዙ ደጋፊ ርእሰ መምህራንና የሚመለከታቸው ባለሙያዎች የተሳተፉ ሲሆን ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉና የአዊ ዞን ተሳታፊ መምህር ለግንቦት ሰባት ዘጋቢ እንደተናገሩት "በ5 ቀናት በተደረገው የግምገማ ስብሰባ እንድንገኝና እንድንወያይ የተጋበዝነው የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን ጥራትና ብቃት ለመገምገም የሚል ይሁን እንጂ በተግባር ስብሰባው ያተኮረባቸው ዋና ርዕሶች በተቃራኒው ባሁኑ ጊዜ ያሉትን አመራር አካላትን በሌሎች አመራሮች መተካት፤ በትምህርት ዘርፍ ያሉትን ያመለካከት ችግሮች መፍታት፤ የተቀናጀ ስራ መስራት፣ መጪውን ምርጫ በሚመለከት ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ነገሮችና ሌሎቹም በትምህርት ዘርፍ ውስጥ አብዮታዊ ዲሞክራሲን ለማስረጽ የተወጠኑ ሃሳቦች እንደነበሩ በምሬት ገልጸዋል።

እኚሁ መምህር የወያኔው አገዛዝ የትምህርት ፖሊሲ የመጻህፍት ጥራትና አቅርቦትን የመምህራን ብቃትና ጥራትን ቦታ የማይሰጥ የግሉን የትምህርት ዘርፍ መጠናከር የማይደግፍ ነገር ግን የይስሙላ ፖሊሲን በወረቀት ላይ በማስፈር በፖለቲካ ወገንተኝነት ላይ ያተኮረ መሆኑን አክለው ገልጸዋል። **(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)**

## የመለስ ዜናዊ ሶስት ምላሶች እና መርዞቻቸው

መለስ ዜናዊ እንግሊዝኛን ለማጭበርበርያ፤ አማርኛን ለአሽሙር፤ ትግርኛን የልቡን ጭንቀት ለማስተንፈሻነት ይጠቀማል። ይህ ሰው "ያለእናንተ እርዳታ መኖር አያቅተንም" ዓይነት መግለጫዎችን በእንግሊዝኛ ሲሰጥ "እርዳታን አግዶ የገዛ ሕዝቡን ለእልቂት ይዳርግ ይሆን?" በሚል ስጋት ምግባረ-ሰናይ ድርጅቶች ለምነውና ተለማምጠው የእርዳታ ምግብና መድሃኒት ያለቁጥጥር እንዲሰጡት ያደርጋል። ከምዕራባዊያን መንግሥታት መልዕክተኞች ጋር ሲነጋገር ደግሞ ከእሱ ቀድሞ ስለዲሞክራሲና የህግ የበላይነት ገለፃ በመስጠት ያደናግራቸዋል። ለውጭ አገራት ወታደራዊና ስለላ ድርጅቶች ደግሞ ከእነሱ በላይ የእነሱ ጥቅም አስጠባቂ ሆኖ በመገኘት ይደልላቸዋል። መለስ እንግሊዝኛን የሚጠቀመው በአክሱምና ላሊበላ የሚገኙ የልምድ የቱሪስት አስጎብኚዎች እንደሚጠቀሙበት አይነት ነው። የልምድ አስጎቢዎቹ ስለሚያስጎበኙት ነገር ያላቸው እውቀት በጣም አነስተኛ ነው። ዓላማቸው ከዚህም ከዚያም የሰሙትን እያጋጩ እጃቸው ውስጥ የገባውን ቱሪስት ማማለልና ደህና ጉርሻ ማግኘት ነው። ስለሆነም የሚያወሩት አጋነውና የሌለውንም ጨማምረው ነው። የመለስ ምላስ ቁጥር አንድ ተግባርም በተመሳሳይ መንገድ የውጭን ዓለም ማጭበርበር ነው። ደጋፊዎቹ ብልህነት ነው ይላሉ። ይህ ብልህነት ከሆነ "ቁጭ በሉ" በመባል የሚታወቁ አጭበርባሪዎች "ጠቢባን ነን" ቢሉ ያስኬዳል።

ምላስ ቁጥር ሁለት በአማርኛ ነው የሚናገረው። ይህ ምላስ ቀና ቃላትን አያውቅም - ሸርዳጅ፣ አሽሟጣጭ፣ አሽሙረኛና ተረበኛ ነው። ይህ ምላስ ፈርተውም ይሁን አክብረው "ፓርላማ" በተሰኘው ሸንጎ በሚጎለቱት የጎሊና ምስኪኖች ላይ ይበረታል። መለስ እዚያ አዳራሽ በተገኘ ቁጥር በዚህኛው ምላሱ ይሞልጫቸዋል። እነሱ "በቃን፣ መረረን" አይሉም፤ እንደማይሉም ያውቃቸዋል። እንዲያውም ይስቁለታል። የመለስ አማርኛ አንዳንችም የጎሊናም ሆነ የባለሙያ ሳንሱር የለበትም። በቴሌቪዝን ቀርቦ "የሚቀሰሩ ጣቶችን እንቆርጣለን?" ባለ ጊዜ "በምን ህግ?" ያለው ሰው የለም። በፓርላማ ውስጥ "ሶማሊያ ውስጥ በኮንዶም አንዋጋም" ብሎ ሲናገር አድማጮቹ ሳቁ እንጂ "እንዲህ አይባልም - ነውር ነው" አላሉትም። ሲለው ደግሞ አማርኛን ለባዶ የተስፋ አዋጅ ይጠቀምበታል። "ከእንዲህ ሶስት ጊዜ እንበላለን"፤ "ከእንግዲህ ከወደሰሜን የጥይት ድምፅ አይሰማም"፤ "እንከን የለሽ ምርጫ እናደርጋለን"፤ "ኢኮኖሚዓችን ዓለምን ባስደነቀ ፍጥነት እያደገ ነው"፤ "የሶማሊያ አክራሪዎችን አከርካሪያቸውን ሰብረናል"፤ "ከእንግዲህ ሻማ ለልደት በዓል ነው የሚበራው" ። በአማርኛ ምን ያላወጀው ነገር አለ፤ አንዱም እውነት ሆኖ አልተገኘም እንጂ !!!!

ምላስ ቁጥር ሶስት የሚያውቀው ትግርኛ ነው። ዋነኛ ሥራውም ብሶትን መግለጽ ነው። በዚህ ምላሱ ብቻ ነው መለስ ለሕዝብ ያለውን አክብሮት የሚገልፀው:: በዚህ ምላሱ ብቻ ነው ስለሕዝብ ታሪክ ሠሪነት የሚያወሳው። በዚህ ምላሱ ለሕዝብ ስላለው ፍቅር ጥልቀት ሲናገር አድማጮችን ያፈዛል "እንደወርቅ የነጠረ"፤ "በእሳት የተፈተነ"፤ "ምርጥ"፣ "ብልህ"፣ "ታጋሽ"፣ "ጀግና" እያለ ያንቆለጳጵሳቸዋል። በዚህ ንግግሩ ሌላው ኢትዮጵያዊ ምን ይሰማው ይሆን ብሎ አይጨነቅም። ሌላ የሚሰማ ሰው ያለም አይመስለው ይሆናል።

በአንድ ራስ ሶስት ምላስ!!! የመለስ ዜናዊን የግል የስብዕና ጉድለት ከዚህ በላይ መግለጫ የሚያሻው አይመስልም። ከፈረንጆች ጋር ሲነጋገር የተስተዋለው መለስ ከኢትዮጵያዊያን ጋር በአማርኛ ሲነጋገር ማግኘት ፈጽሞ አይቻልም። ልክ አማርኛ መናገር ሲጀምር ተረበኛውና አሽሙረኛው መለስ ነው የሚመጣው። ትግራይ ሲሄድና በትግርኛ ሲናገር ደግሞ ከሁለቱም ውጭ የሆነ ሌላ መለስ በተራ አለባበስ ብቅ ይላል። ይህን ሰው ምን ይሉታል?

ለምሳሌ በቅርቡ መቀሌ ውስጥ ያደረገው ንግግር "መለስ" ስለ ተሰኘው አውሬ ብቻ ሳይሆን ከዚያም ባለፈ ስላሉ ጉዳዮች የሚያስገነዝቡን ነገሮችን ይዞዓል። ሌላ ሰው ቢናገራቸው ኖሮ እድሜ ልክ የሚያስፈርዱ ነገሮችን እሱ በአደባባይ በእልልታና በጭብጨባ ታጅቦ ተናግሯቸዋል። ተቃዋሚዎች ወያኔን "ገዢው ፓርቲ" እያሉ በአክብሮት መጥራት ሲኖርባቸው መለስ መቀሌ ውስጥ በትግርኛ "ጠላቶቻችን" ብሎዓቸዋል። ለዚህም እልልታ ተችሮታል። መሰሪነቱን እየተረዱ ሸሸት ያሉትን የቀድሞ ጓዶቹን "ጭቃዎች"፣ "እንክርዳዶች"፣ እርጋፊዎች" እያለ ሲወርድባቸውም ተጨብጭቦለታል። ከእነዚህ ቃላት አንዱን እንኳን ሌሎች ተናግረውት ቢሆን ኖሮ በዘር ማጥፋት፣ አመፅን በማነሳሳት እና ህገ-መንግሥቱን በመናድ ተደራራቢ ወንጀሎች ተከሰው ብዙ የእድሜ ልክ እስራቶች በተፈረዱባቸው ነበር። እሱ ግን በሁለት ምክንያቶች ስጋት የለበትም - አንድ እሱ በመሆኑ፤ ሁለት በትግርኛ መናገሩ። ይህንን የትግራይ ሕዝብ እንዴት ያየዋል?

በመለስ የመቀሌው ንግግር ትግርኛ አንድ እርከን ተሸጋግሯል። ትግርኛ በአደባባይ ሳይቀር የአፈና መመሪያ መስጫ የኮድ ቋንቋ ሆኗል። "እባካችሁን ለእነዚህ ጭቃዎች ጉልበት አታሳዩዓቸው" ሲል አስፈፃሚዎቹ "እያደናችሁ ቀጥቅጧቸው" ማለቱ እንደሆነ ገብቷቸው ወዲያውኑ መመሪያውን ተግባራዊ ማድረግ ጀምረዋል። እንዲያውም ይህን ባለ በቀናት ውስጥ ከድብደባ አልፈው እመግደል ድረስ ደርሰዋል - እዚያው ትግራይ ውስጥ!!!

የመለስ ሶስቱም ምላሶች መርዘኞች ናቸው። ትግራይና የትግራይ ሕዝብ የዚህ መርዘኛ አውሬ መሸሸጊያ መሆኑ ማብቃት ይኖርበታል። ትግርኛ የኢትዮጵያ ቋንቋ ነው፤ ሊከበር ይገባዋል። ትግርኛ የገራፊዎች፣ የጆሮ ጠቢዎችና የሙሰኞች ቋንቋ መደረጉ መብቃት አለበት እንላለን። ወያኔ ኢትዮጵያን ለማጥፋት የተነሳ ኃይል ነው። በተለመደ አጭበርባሪነቱ ይቅጠፍ እንጂ ለኢትዮጵያ የማይበጅ አካሏ ለሆነችው ትግራይም እንደማይበጅ ሃቅ ነው።

ስለሆነም ሁላችንም የወያኔን እድሜ ለማሳጠር እና ፍትህ፣ ነፃነትና እኩልነት የሰፈኑባት ኢትዮጵያን ለመገንባት ታጠቀን እንነሳ!!!

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ**

## መለስ ዜናዊ በወ/ት ብርቱካን ጉዳይ . . . ከገጽ 1 የዞረ

እስር ቤት እንዲገቡ እንደሚያደርግ ተደጋግሞ የተባለ ጉዳይ ሲሆን፣ ለስልጣኑ ከማያሰጉት ደካማ ፓርቲዎች ጋር ደግሞ የምርጫ ስምምነት በሚል የይስሙላ ሰነድ በማስፈረም ለማታለል እየሞከረ ነው።

በተያያዘ ዜናም አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ እየታየ ያለው የሰብአዊ መብት ጥሰት የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልኡካንን ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ በሚያሳርፈው ውሳኔ ላይ ከፍተኛ ተጽኖ እንደሚኖረው አንድ የምእራብ ዲፕሎማት ተናግረዋል። ዲፕሎማቱ ለግንቦት7 ዘጋቢ እንደገለጹት አሁን የሚታየው የሰብአዊ መብት ጥሰት የአውሮፓ ህብረትም እንደ ካርተር ማእከል አይነት ውሳኔ እንዲወስን ያስገድደው ይሆናል ካሉ በሁዋላ፣ የስብአዊ መብት ጥሰቱ በዚሁ ከቀጠለ ኢትዮጵያ ወደ አልታሰበ ችግር ትገባለች ብለዋል።

በሌላ ዜና ደግሞ የአዲስ አበባ ህዝብ ለምርጫው የሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን አሁንም የወያኔን ባለስልጣናት እንቅልፍ ነስቶአቸዋል። ወያኔ ያለ የሌለ ሀይሉን ተጠቅሞ የአዲስ አበባ ህዝብ ለምርጫ እንዲመዘገብ ለማድረግ ቢሞክርም፣ በምርጫው ለመሳተፍ የተመዘገበው ህዝብ ግን እጅግ አነስተኛ መሆኑን ለማወቅ ተችሎአል። ብዙዎች የአዲስ አበባ ህዝብ የ97ቱን ምርጫ በቀላሉ ሊረሳውና በጊዜው ያቀረባቸው ጥያቄዎች እስካሁን ባለመመለሳቸው ነው የሚሉ አስተያየቶችን የሚሰጡ ሲሆን የመኢአዱ ሊ/መንበር አቶ ሀይሉ ሻውል ግን ይህን ሀሳብ ተቃውመውታል። አቶ ሀይሉ ለአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ በሰጡት ቃለምልልስ ምንም እንኳ የአዲስ አበባ ህዝብ በምርጫው በብዛት አለመመዝገቡ እውነት ቢሆንም፣ ያልተመዘገበበት ምክንያት ግን ለክልል ምክር ቤት ምርጫ ስለማይደረግ ነው ብለዋል። አቶ ሀይሉ እንደሚሉት የአዲስ አበባ ህዝብ ለፓርላማ ምርጫ ያን ያክል ትኩረት ባለመስጠቱና ትኩረቱም በክልል ምርጫ ላይ በመሆኑ በምርጫው ለመሳተፍ ፈቃደኛ አልሆነም።

በአቶ ሀይሉ አስተያየት የተገረሙት አንድ የመድረክ ተቃዋሚ አባል እንደተናገሩት " አቶ ሀይሉ በአዲስ አበባ ህዝብ ዘንድ ፓርቲያቸው ያለውን ድጋፍ ስለሚያውቁ በህዋላ ከሚመጣባቸው ችግር ከአሁኑ መከላከያ እያበጁ ነው" ያሉ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ፓርቲያቸው የከፋ ችግር እንዳልገጠመው የተናገሩት ብዙዎችን ባልደረቦቻቸውን እንዳስገረመ ለማወቅ ተችሎአል። አቶ ሀይሉ በአሁኑ ጊዜ ግልጽ የሆነ የፖለቲካ አቋም ለመያዝ መቸገራቸውን በተደጋጋሚ በሚሰጡት ቃለምልለስ ለማየት የሚቻል ሲሆን፣ በእዚህ አቋማቸው አብረዋቸው ሲታገሉ የነበሩ ሰዎች ጭምር እየሸሹዋቸው መምጣታቸውን ለማወቅ ተችሎአል። አቶ ሀይሉ እስር ቤት በነበሩበት ጊዜ የመኢአድ ቀን እጅ ተደርጋ ትቆጠር የነበረችው ወ/ሮ መሰበወርቅ ፣ በድርጅቱ ውስጥ ባለው ፖለቲካ በመበሳጨት እራሱዋን ከፓርቲው ማግለሉዋ ይታወቃል።

## የወያኔ ካድሬ መምህራን ሳይቀሩ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ቀጥለውም ከዚህ በፊት የምናደርገው የስራ ግምገማም ቢሆን ምን ያህል ቅስቀሳ ተደርጎ ምን ያህል ተማሪ ተመዘገበ? የተማሪው ብዛት ስንት ደረሰ? ለምን የተማሪ ቁጥር ቀነሰ? የመምህራን የፖለቲካ አቋም ምንድነው? ያመለካከት ቺግር አለ ወይ? በሚሉና ተመሳሳይ በሆኑ ጥያቄዎች ዙሪያ ያተኮረ እንጂ የትምህርት ጥራትን እንዴት እናምጣ? የሚባል ሃሳብ ይንጸባረቅ እንዳልነበርና በዚህም ምክኒያት ተማሪዎች ክፍልን የመቁጠር እንጂ እውቀትን የመጨበጥ ሂደት እንደሌላቸው ገልጸዋል።

በተግባር እየሆነ ያለውን ሳስብ ያስፈራኛል የሚሉት መምህሩ ያስተማርናቸው ልጆቻችን የዲግሪ ሰርቲፊኬትን ያዙ ይባል እንጂ በዚህ ደረጃ ላይ ተቀምጠው ራሳቸውን ለመግለጽ እንኳ ችግር አለባቸው ሲሉ በሀዘን ተናግረዋል። ባሁኑ ጊዜ የትምህርት ዘርፉን በባለቤትነት የሚመራውን ክፍል ነጻነት በመግፈፍ ወያኔ ባንዳንድ ክልሎች ከአንደኛ እስከ መሰናዶ ያሉትን ትምህርት ቤቶች የቀበሌ አስተዳደር በሚባለው የአገዛዙ መዋቅር ስር እንዲሆኑ መደረጋቸውንም መምህሩ ጠቁመዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ለመምህርነት ስልጠና የሚታጩት ወጣቶች የሚመለመሉት የፖለቲካ ወገንተኝነትን፤ ቁርጠኝነትንና ለአገዛዙ ያላቸውን ታማኝነት እንደ ዋና መስፈርት በመውሰድ እንጂ ያላቸውን የትምህርት እውቀትና ብቃት ታሳቢ በማድረግ ባለመሆኑ በተለያዩ ተቋማት እየሰለጠኑ የሚወጡ ወጣቶች ብቃት አሳዛኝ መሆኑንና በትምህርት ጥራት ላይም እያሳደረ ያለውን ተጸኖ ለመግለጽ ከሚያሳፍር ደረጃ ላይ መድረሱን እኚሁ የስብሰባው ተሳታፊ መምህር ገልጸዋል።

በአዲስ አበባ የሚኖሩ አንድ የሁለተኛ ደረጃ መምህር ደግሞ "የወያኔው አገዛዝ በትምህርት ዘርፍ ያለው የሰው ሃይል በሙሉ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ አቅጣጫ እንዲያስብ ለማድረግ ዛሬም ድረስ እየጣረ ነው፣ ለዚህም ዋቢ የሚሆነው ላለፉት በርካታ አማታት በክረምት የእረፍት ጊዜ በየክልሉ ለመምህራን፤ ርሳነ መምህራንና ከትምህርት ዘርፍ ጋር ለሚቀራረቡ ሰራተኞች ሁሉ የትምህርት ጥራትን ሰበብ በማድረግ የ15 ቀናት የአብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ጸበል የተቋዳሽነት ስልጠና መሰጠቱ ነው ሲሉ ተናግረዋል። በመጨረሻም እኔ የእንጀራ ጉዳይ ሆኖብኝ በዚህ ሂደት ውስጥ ተሳታፊ በመሆኔና ባሁኑና በወደፊቱም ትውልድ ላይ እየተፈጸመ ላለው በደል ተባባሪ በመሆኔ ጸጸት አለብኝ ሲሉ ገልጸዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ወያኔ አዲስ አበባችንን እንዴት ንጹህ እናድርጋት በሚል ሰበብ መምህራንን ለስብሰባ ከጠራ በሁዋላ፣ ስለመጪው ምርጫ ተሳትፎ ማውራቱ ብዙዎችን እንዳሳዘነ ሪፖርተራችን ገልጿል። በርካታ መምህራን በሁኔታው ተገርመው ጥያቄዎችን ማቅረባቸው ሲገለጽ፣ አንዳንዶችም ምርጫው በኢህአዴግ አሸናፊነት እንደሚጠናቀቅ እየታወቀ፣ ይህን ያክል መጨነቁ ለምን አስፈለገ ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። የወያኔ ባለስልጣናት በበኩላቸው "ከምርጫው ውጤት ይልቅ ሂደቱ ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን እንፈልጋለን፣ የምርጫው ውጤት በምርጫው ሂደት ላይ ተመስርቶ የሚመጣ በመሆኑ መምህራን ሰፊ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል" የሚል መልስ ሰጥተዋል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፡- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 94 የካቲት 25 2002 ዓ.ም፤ ገጽ.3

## አድዋ ትናንት እና ዛሬ

የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ፣ የዛሬ 114 አመት መሆኑ ነው፣ በአፍሪካ ምድር ያልታየ አዲስ ታሪክ በኢትዮጵያ ምድር ተሰራ። እለቱ በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ የፈረሰኛው ጊዮርጊስ ወርሀዊ በአል የሚከበርበት ቀን በመሆኑ ፣ ኢትዮጵያውያን ፈረሰኛው ጊዮርጊስ ከታንከኛው የጣሊያን ጦር እንደሚታደጋቸው ምንም ጥርጥር አልነበራቸውም። የሚኒሊክ የመረጃ ክፍል የሆነ አንድ ወጣት እየተንደረደረ መጥቶ ለንጉስ ሚኒልክ ጌታየ "ባራቴሪ" ተኩስ ከፍታብናለችና ቶሎ ብለው አንድ ነገር ያድርጉ በማለት ሹክ ሲላቸው ፣ ሚኒሊክና ሰራዊታቸው ጸሎታቸውን ለ" ፈረሰኛው ጊዮርጊስ" አድርሰው ዘመናዊ መሳሪያ እስካፍንጫው የታጠቀውን የጠቅላይ ሚኒስትር ክርስፒን ጦር ለመግጠም ቤተክርስቲያኑዋን ለቀው ወጡ።

ጣሊያን እንዳገር አንድ ሆና ገና ከመቁዋቁዋሟ፣ የታላቂቱን የሮማ የግዛት ታሪክ እያስታወሰች አዲሲቷን ሮማን በአዳዲስ ቅኝ ለማስፋት ማውጠንጠን ጀመረች። እንደ እንግሊዝና ፈረንሳይ የመሳሰሉት ሀያላን መንግስታት በርካታ ቅኝ ተገዢ አገሮችን ለመያዝና ለማስተዳደር በመቻላቸው፣ በአውሮፓ ውስጥ የነበራቸው ተሰሚነትና ክብር በእጅጉ ከፍ ያለ ነበር። አዲስቷ ጣሊያን ሲሆን ሲሆን ጥንታዊቷ ሮማ ከደረሰችበት ከፍታ ለመድረስ ፣ ካልሆነም ግን እንግሊዞችና ፈረንሳዮች ካላቸው ክብር የሚስተካከል ክብር ለመገንባት በርካታ ቅኝ ተገዢ አገሮችን መያዝ እንዳለባት አምናለች። ቅኝ የሚገዙ አገሮችን መያዝ ከሚያስገኘው ክብር በተጨማሪ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታም ነበረው። በአንድ በኩል አውሮፓኖች በማደግ ላይ ለነበረው እንዱስትሪያቸው ግብአት የሚሆኑ ጥሬ እቃዎችን ከእነዚህ ቀኝ ተገዢ አገሮች ያገኛሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለሚያመርቱት እርካሽ የእንዱስትሪ ምርቶች ገበያዎችን ለማግኘት ይረዳቸዋል። እናም የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች በማታላል ወይም በማስፈራራት ከበርካታ የአፍሪካ የጎሳ መሪዎች ወይም ነገስታት ጋር ውሎችን እየተዋዋሉ ቅኝ ግዛታቸውን ለማስፋፋት ችለዋል። ውሎችን ለመዋዋል ፈቃደኛ ያልሆኑ የአፍሪካ ነገስታትን ሲያገኙ ደግሞ በሀይል ለማንበርከክ ጦርነትን እንዳማራጭነት ተጠቅመዋል። ጣሊያንም ወደ ምስራቅ አፍሪካ በመሄድ ግዛቱዋን ለማስፋፋት ስታስብ ቢቻል በሰላም ካልተቻለም በሀይል ለመጠቀም ወስና ነበር። በእርግጥ ጣሊያን ወደ ምስራቅ አፍሪካ ከመዝመቷ በፊት የሚዲትራኒያንን ባህር የሚያካልሉ አገሮችን የመቆጣጠር ምኞት ነበራት። ይሁን እንጅ እነዚህ አገሮች አስቀድመው በፈረንሳይና በእንግሊዝ ተይዘው ስለነበር፤ ጣሊያን በአማራጭነት ለሚዲትራኒያን ቅርብ የሆኑትን የቀይ ባህር አካባቢዎች ለመቆጣጠር ታጥቃ ተነሳች።

የጣሊያን የመስፋፋት ዘመቻ የመሰረት ድንጋይ የተጣለው አሰብ ላይ ነበር። ሩባቲኖ የተባለ የጣሊያን የመርከብ ድርጅት በወቅቱ የአሰብ ግዛት አስተዳደሪ ከነበሩት ሱልጣን ወደቡን በ9 ሺ ዶላር ገዛ። በሁዋላ ግን የጣሊያን መንግስት ወደቡን ወደ ተቀረው የኢትዮጵያ ክፍል ለመረማመጃነት እንደሚጠቀምበት በማመኑ፣ ከዚሁ ኩባንያ ወደቡን በ43 ሺ ዶላር ገዛው። ጣሊያንም አሰብን መያዙዋ እንደታወቀላት በቀጥታ አፍሪካን ለመቀራመት አላማ ካደረገው የበርሊን ጉባኤ እንድትሳተፍ ተደረገ። የጉባኤው ተሳታፊ አገሮችም ጣሊያን ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት እንድትይዝ ፈቃድ ሰጡ። ከዚያ በሁዋላ የጣሊያን መንግስት ኢትዮጵያን ለማንበርከክ ታጥቆ ተነሳ።

ጣሊያን ከባዱን የአድዋ ጦርነት ከማካሄዷ በፊት በርካታ መለስተኛ የሆኑ ጦርነቶችን ከኢትዮጵያውያን ጋር ስታደርግ ቆይታለች። እነዚህ ጦርነቶች ግን ሁሌም በጀግኖቹ የኢትዮጵያ መሪዎች አሸናፊነት ይጠናቀቁ ነበር። በተለይ የራስ አሉላና የአጼ ዮሀንስ ሚና ምንጊዜም ተጠቃሽ ነው።

አጼ ሚኒልክ የኢትዮጵያ ገዢ መሆናቸው ሲረጋገጥ የውጫሌ ውል እየተባለ የሚጠራውን ውል ከጣሊያኖች ጋር እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1889 ዓም ተፈራረሙ። ውሉ በኢትዮጵያና በጣሊያን መካከል መልካም የኢኮኖሚና የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ለመመስረት አላማ አድርጎ የተፈረመ ቢሆንም፣ ጣሊያኖች በፈጸሙት ደባ ውሉ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት የሚጻረር አንቀጾች ነበሩት። በተለይ በአንቀጽ 17 ላይ የሰፈረው ስምምነት ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ በጣሊያን ቅኝ ግዛት ውስጥ የሚያስገባ ነበር። ይህ አንቀጽ በአማርኛው ቅጅ ላይ የሚከተለውን አሰፍሯል "ኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት በምታደርግበት ጊዜ የጣሊያንን መንግስት እገዛ ከፈለገች ጣሊያን የኢትዮጵያን ፈቃድ ለመፈጸም ፈቃደኛ ነች።" ይሁን እንጅ በጣሊያንኛ ቁዋንቁዋ በተፈረመው ቅጅ ላይ ያለው ስሜት ከዚህ በተለየ ቀርቦአል "ኢትዮጵያ ማንኛውንም አይነት የውጭ ግንኙነት በጣሊያን መንግስት በኩል ታደርጋለች።" ይላል። በጣሊያን ልኡካን እንደተጭበረበሩ የገባቸው አጼ ሚኒሊክ ወዲያውኑ ስምምነቱ እንዲፈርስ ጠየቁ።

በጊዜው የጣሊያን ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው ክርስፒ ግን ጉራና ንቀት በተሞላበት ሁኔታ ኢትዮጵያ ከዛሬ ጀምሮ በጣሊያን ስር ነች እያለ ከማወጅ በስተቀር ውሉን ለማስተካካል የሚያስችል እርምጃ አልወሰደም ነበር። ይባስ ብሎም ኤርትራን በመውረር የመጀመሪያዋ የጣሊያን ቅን ግዛት አገር ተመሰረተች ብሎ በ1890 ዓም አዋጅ አስነገረ። እንግሊዝም ሳትውል ሳታድር ጣሊያን ላቀረበችው ሀሳብ ድገፉዋን ሰጠች። የጣሊያንና የሌሎች ከሩስያና ከቱርክ መንግስታት ጋር ያላቸውን ግንኙነት በማጠንከር፣ መንግስታትተንኮል ያበሳጫቸው አጼ ሚኒሊክ፣ ወዲያውኑ ከጀርመን፣ ጣሊያንን ለመፋለም ወስነው ዝግጅት ጀመሩ። እንዲህም ሲሉ ለህዝባቸው ተናገሩ " እግዚአብሄር በቸርነቱ ጠላቶቼን ድባቅ መትቶልኝ፣ ግዛቴንም አስፍቶልኝ፤ እስከዛሬ ድረስ አቆየኝ። በእግዚአብሄር ጸጋም ነግሻለሁ። ጠላት አገራችንን ለመውረር ሀይማኖታችንንም ለማስለወጥ ደጃፋችን ድረስ መጥቷል። እግዚአብሄር ድንበር ይሁናችሁ ብሎ የሰጠንን ባህር እየተሻገረ እንደፍልፈል መሬት እየቆፈረ በመስፈር ላይ ነው። በእግዚአብሄር ሀይል ድባቅ መትቼ አጠፋቸዋለሁ።"

በጣሊያን የመስፋፋት ፍላጎትና በኢትዮጵያ የነጻነት ፍላጎት መካከል ያለው ክፍተት እየሰፋ በመሄዱ የሁለቱ አገሮች ፍላጎት ሊታረቅ የሚችለው አንዱ አሸንፎ ሌላውን በማስገደድ ፍላጎቱን እንዲቀበል ሲያደርገው ብቻ ነው። ጣሊያን ጄኔራል ባራቴሪ ለተባለው የጦር መሪዋ የቀይ ንስር የተባለውን ከፍተኛ ወታደራዊ ማእረግ በመሸለም፣ አቢሲኒያን እንዲያንበረክክ ፈቃድ ሰጠች። ጄኔራል ባራቴሪም ከ20 ሺ በላይ የሚሆነውን ጦሩን ይዞ፣ 100 ሺ የሚሆነውን የኢትዮጵያን ጦር ለመግጠም ጦሩን በሶስት ማእዘን አንቀሳቀሰ። በጄኔራል ዳቦር ሜዳ የሚመራው ጦር የበለሀ ተራሮችን በቀኝ በኩል አጥሮ እንዲይዝ፣ የጄኔራል አርሞንዲ ጦር ደግሞ በመሀል ሰንጥቆ እንዲገባ ታዘዘ። ጄኔራል አልቤርቶኒ በበኩሉ የኪዳነምህረት ታራራን እንዲቆጣጠር ትእዛዝ ቢሰጠውም፣ እንዳ ኪዳነምህርትና ኪዳነምህረት የሚባሉት ሁለቱ ቦታዎች ስለተምታቱበት፣ ከኪዳንምህረት ተራራ ሳይደርስ በሌላ ቦታ ላይ ሰፈረ በጄኔራል ኢሊና የሚመራው ጦር ደግሞ ከጄኔራል ባራቴሪ ጦር ጋር በመሆን በተጠባባቂነት እንደቀመጥ ተደለደለ።

የኢትዮጵያ ጦር አሰላለፍ ደግሞ የሚከተለውን መሰለ። የጎጃሙ ንጉስ ተክለሀይማኖት እግረኛና ፈረሰኛ ጦር በአካባቢው የሚገኙትንና ጣሊያን ምሽግ የሰራባቸውን ተራሮች በቀኝ በኩል አጥሮ እንዲይዝ ታዘዘ። የራስ መኮንን ጦር ደግሞ በአድዋ ከተማ ላይ እንዲሰፍር ተደረገ። ራስ ሚካኤል ጦራቸውን ይዘው በሰላዶ ተራራ አካባቢ ባለው የግራ ክፍል ላይ እንዲጠባበቁ ተደረገ። የራስ መንገሻ ጦርም በራስ ሚካኤል አካባቢ ባለው ዝቅተኛ ቦታ ሆኖ ጣሊያንን እንዲገጥም ተደለደለ። የራስ አሉላ ጦር አዲ አቡና በሚባለው ተራራማ ክፍል ሲሰፍር በአጼ ሚኒልክ እና በእቴጌ ጠሀይቱ የሚመሩት ክፍሎች ደግሞ አማካኙን ቦታ በመያዝ በተጠባባቂ ጦር እንዲያገለግሉ ተመደቡ።

በኢትዮጵያ ወገን ከተሰለፈው ጦር ውስጥ 20ሺ የሚጠጋው ሰራዊት ጠመንጃ የሚባል ነገር አልነበረውም። በከባድ መሳሪያ በኩል የኢትዮጵያ ጦር 40 መድፎች ቢኖሩትም የጣሊያን ጦር በአድዋ ብቻ ያለፈው የመሳሪያ ብዛት ከ60 አያንስም ነበር።

በጄኔራል ባራቴሪ የሚመራው ሰራዊት ሌሊቱን በሶስት ተከፍሎ የኢትዮጵያን ጦር በድንገተኛ ሁኔታ ለማጥቃት በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ፣ መንገድ እየጠፋበት ተቸገረ። ለምሳሌ በጄኔራል አልቤርቶኒ የሚመራው ጦር እየተደናበረ ሲሄድ በድንገት ኢትዮጵያውያን ከሚገኙበት ሰፈር ደረሰና የአድዋው ጦርነት ተጀመረ። የጄኔራል አልቤርቶኒ ጦር ባላሰበው መንገድ ከባድ ውጊያ ውስጥ መውደቁን ጄኔራል ባራቴሪ እንደተረዳ፣ ወዲያውኑ ለጄኒራል ዳቦር ሜዳ ትእዛዝ በማስተላለፍ ጄኔራል አልቤርቶኒ የሚረዳበትን መንገድ አመቻቸ። ይሁን እንጅ ጄኔራል ዳቦር ሜዳ ከአዛዡ ከጄኔራል ባሪያቴሪ የተሰጠውን ትእዛዝ ትቶ በቀኝ በኩል ግስጋሴውን አደረገ። ሁለቱ ጄኔራሎች በፈጸሙት ስህተት የተፈጠረውን ክፍተት ተጠቅመው ራስ መኮንን ጦራቸውን ወደ መሀል አስገቡ። የኦሮሞ ፈረሰኛ እባል ጉሜን እየጨፈረ የጣሊያንን ሰራዊት ማራወጥ ያዘ። ራስ ተክለሀይማኖት በቀኝ፣ ራስ አሉላ በግራ፣ ራስ መንገሻና ራስ መኮንን በመሀል ያለውን ጦራቸውን ክተት ብለው ከጣሊያን ጋር የሚያደርጉትን ፊልሚያ ቀጠሉ። ምድር ቁና ሆነች። የጣሊያን ጦር ይዞት የመጣውን ዘመናዊ መሳሪያው ዘመናዊ መሳሪያ ባልታጠቁ ኢትዮጵያውያን ላይ መሞከር ጀመረ። ኢትዮጵያውያኑ ግን ለመድፍ የሚበገሩ አልሆኑም። "ይህ ነው ምኞቴ እኔ በህይወቴ ከራሴ በፊት ለኢትዮጵያ እናቴ" ብለው ከራሳቸው በፊት ኢትዮጵያን አስቀደሙ።

ጦርነቱ ቀጠለ። የድል ብስራቱም መሰማት ጀመረ። ጄኔራል አልቤርቶኒ ለሁለት ሰአታት ያክል በጀግንነት ከተዋጋ በሁዋላ እጁን ለንጉስ ተክለ ሀይማኖት አስረከበ። ይህም የኢትዮጵያውያንን ሞራል ከፍ አደረገው። አከታትሎ ደግሞ ጄኔራል አርሞንዲ መገደሉ ተሰማ። በጣሊያን ዘንድ ሽብር ነገሰ። ለውጊያ ከተላኩት ውስጥ የቀረው ጄኔራል ዳቦር ሜዳ ብቻ ነው። እርሱም ቢሆን የማታ ማታ ነገሩ አላምርህ ሲለው ለማምለጥ ሞከረ። ይሁን እንጅ ውሀ ውሀ እንዳለ ይህችን ምድር ተሰናበተ።

ወደ አመሻሹ ላይ፣ የኢትዮጵያ ድል በአለም ላይ ሁሉ ተናኘ ። በጥቁር ህዝቦች ዘንድ ፈንጠዝያ ሆነ። በአለም ላይ ሁሉ ኢትዮጵያ የነጻነት ተምሳሌት ሆነች። የዛሬውን አያድርገውና አፍሪካዊው ሁሉ ኢትዮጵያዊ ነኝ ማለት ጀመረ። በደቡብ አፍሪካ ፣በላቲን አሜሪካ፣ በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ የነበሩ ጥቁሮች የነጻነት ትግሎችን ለማካሄድ የሞራል ግፊት አገኙ።

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየው ፈንጠዝያም ጨምሮአል። አሮሞው፣ አማራው፣ ትግሬው፣ አገው፣ አፋሩ፣ ሶማሊው በአጠቃላይ ኢትዮጵያዊው ሁሉ በተገኘው ድል ሰከረ። ደማቅ ታሪኩንም በዘላለማዊ ብእሩ ጻፈ።

### አጭር መልእክት

እጅግ የሚያሳዝነው ዛሬ ይህ ደማቅ ታሪክ፣ በጥቂት የባንዳ ተወላጆች ሲደለዝ እየተመለከትን ነው። ሚሊዮኖች ደማቸውን አፍስሰው አጥንታቸውን ከስክሰው ያቆዩአትን አገር፣ ባንዳዎች እየቸበቸቡዋት ነው። አጼ ዮሀንስ ለዳር ድንበራቸው መከበር ሲሉ አንገታቸውን ለደርቡሽ የሰጡበት ታሪክ ተረስቶ፣ መሬት ለሱዳን በገፍ እየተሰጠ ነው። በቅኝ ግዛት ጊዜ እንደነበረው ዛሬ የአገራችን ደሀ ገበሬ ከመሬቱ እየተፈናቀለ መሬቱ ለአዳዲሶቹ ተረኛ ቅኝ ገዢዎች እየተሰጠ ነው። አባቶቻችን የተፋለሙት አፍሪካን ለመቀራመት ህልም ከነበራቸው ያውሮፓ አገሮች ጋር ነበር። የዛሬዎቹ አሳፋሪ ገዢዎች ላረብና ለእስያ መንግስታት በጥቂት ሳንቲሞች የአገራቸውን መሬት እየቸበቸቡ ነው። ከ114 አመት በሁዋላ አገራችን በአዲሶቹ ቅኝ ገዢዎች ስር እየወደቀች ነው። ይህን የሚያስፈጽም የባንዳ ሀይል ደግሞ ስራውን በፍጥነት እየሰራ ነው።

የአገራችን ወጣቶችና የመከላከያ ሰራዊታችን እነዚህን የባንዳ ስብስቦች በማባረር ኢትዮጵአን ከባንዳ አገዛዝ ነጻ የማውጣት ሃላፊነት አለባቸው። በጀግንነት የተሰውት አባቶቻችንም በዛሬ ቀን እያስተላለፉልን የሚገኘው አገርክን ክብሩዋን ከሚያዋርዱ ባንዳዎች ተጠንቀቅ የሚል ነው።

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር።**

## በኢትዮጵያ ወስጥ የሚታየው የሰባአዊ መብቶች ረገጣ እና አምባገነንነት አገሪቱን ለከፋ ችግርና ለግጭት ሊዳርጋት እንደሚችል የበርካታ ኢትዮጵያዊያንን አስተያየት አሰባስቦ ቢቢሲ ዘገበ

ቢቢሲ ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ባቀረበው ሰፊ የዜና ሃተታ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየው የሰብ ዓዊ መብቶች ረገጣ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ መሆኑን አመልክቶአል። ይህ የአምባገነንነት ስርአት በአገሪቱና በዜጎቿ ላይ እየፈጸመ ያለው ሰቆቃ አጋሮቹ የሆኑትን የውጪ መንግሥታት በተለይም ለወያኔው አገዛዝ ከፍተኛ የገንዘብና የፖለቲካ ድጋፍ የምትሰጠውን እንግሊዝ ተጠያቂ እንደሚያደርግ ቢቢስ በዘገባው አመልክቶአል። በጸረ ሽብር ትግል ሥም አምባገነኑን አገዛዝ ለመደገፍ የሚደረገው ጥረት ኢትዮጵያን አንደ ጎረቤት ሱማሊያ እና ሱዳን ከፍተኛ ወደ ሆነው የርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ሊከታት እንደሚችል መሁራንን ጠቅሶ የዘገበው ቢቢሲ ችግሩ በጊዜ ካልተፈታ በቀር ኢትዮጵያ ለሚገጥማት ከፍተኛ አደጋ የአለም አቀፍ መንግሥታት ተጠያቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ አሳስቦአል።

የኢትዮጵያ ሰብ ዓዊ መብቶች ጉባ ኤ ኢሰመጉ ሊቀመንበር የሆኑት ዶር ታዬ አሰፋ ለጋዜጠኛው እንደተናገሩት የወያኔ አገዛዝ በአገሪቱ ውስጥ የነበረውን ብቸኛ የሰባአዊ መብቶች ተከላካይ ድርጅታቸውን ሳይቀር ለማፍረስ የወሰደውን እርምጃ በመተንተን ካስረዱ ቦኋላ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየው የመብት አፈና በርካታ ዜጎችን ወደ አመጽ ትግል ሊወስዳቸው እንደሚችል በቂ ምልክቶች እየታዩ ነው ማለታቸውን ዘግቦአል።

የአውራ አምባ ታየምስ አሳታሚ አቶ ዳዊት ከበደ በበኩሉ የወያኔው አገዛዝ የፕረስ ነጻነትንና ሃሳብን የመግለጽ መብት ለማፈን እየወሰደ ያለው እርምጃ ተስፋ አስቆራጭ እየሆነ መምጣቱን ጠቅሶ በዘንድሮው ምርጫ የጋዜጦች ተሳትፎ ሙሉ በሙሉ እንዲገታ በመደረጉ ወያኔ ያለማንም ተቀናቃኝ ምርጫውን ለማሸነፍ ያስችለዋል ብሎአል። ወያኔ በአገሪቱ ውስጥ ጋዜጦች በነጻነት እየተሰራጩ ነው ብሎ ስለሚለፍፈው ተራ ፕሮፖጋንዳ አቶ ዳዊት ሲናገር በአሁኑ ጊዜ ያሉት ጋዜጦች በነጻነት ለመሥራት በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ እንደገቡና ባለው ፍራቻ ምክንያት እራሳቸውን በቅድመ ምርመራ ወይንም በ እንግለዘኛው አጠራር ሴንሰር እያደርጉ እንደሚዘግቡ ፤ ለአብነትም እሱ ራሱ በአሁኑ ጊዜ 6 የተለያዩ ክሶች ተመስርቶበት ፍርድ ቤት እየተመላለሰ እንደሚገኝ ገልጾአል።

አንድ የፓርላማ አባል በበኩላቸው ለምርጫ ለመወዳደር ምዝገባ በሚያደርጉበት ወቅት ድብደባ እንደተፈመባቸው ገልጸው፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላማዊ ትግል የማድርጉ ትስፋ እየተማጠጠ መምጣቱን በምሬት ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ የእንግሊዝ አምባሳደር ችግሩ መኖሩን ቢያምኑም፣ አገራቸው በወያኔ አገዛዝ ላይ እርምጃ ለመውሰድ አለመዘጋጅቱዋን ተናግረዋል።

የወያኔው ተላላኪ አምባሳደር ተብየው ብርሀኑ ከበደ፣ ከ20 አመት አገዛዝ በሁዋላ አሁንም ለዲሞክራሲ አዲስ ነን የሚል ምልስ ሰጥቷል።

## የወያኔው አገዛዝ በተቀናቃኞቹ ላይ ግድያ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

እንዳስላሴ አካባቢ በአጽበደ ጻቢላ ከተማ መድረክን በመወከል ጠንካራ እንቅስቃሴ እያደረጉ የነበሩትን አቶ አረጋዊ ገብረ ዮሃንስን በስድስት ታጣቂዎቹ አስደብድቦ ማስገደሉን ለማወቅ ተቺሏል። በተመሳሳይ ሁኔታም በአክሱም አካባቢ በምትገኘው ውቁሩ ማሬይ ከተማ መድረክን በመወከል ለመወዳደር የተመዘገቡትን አያሌው አየለ የሚባሉ አባል በተመሳሳይ ሁኔታ በታጣቂዎች ማስደብደቡን ግለሰቡም በሞትና ህይወት መካከል የምገኙ መሆኑ ተዘግቧል።

ይህን ዜና አስመልክቶ ያነጋገርናቸው አንድ ስማቸው እንዳይገለጽ የጠየቁ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል በሰጡት አስተያየት የወያኔው አገዛዝ ምናልባት ቀደም ብሎ ከነበረው ከ1997 ምርጫ በተለየ መልኩ ባሁኑ ሰዓት ገና ከጠዋቱ የማስፈራሪያና ህዝብን የማሸማቀቂያ የግድያ ርምጃ መውሰድ ይጀምር እንጂ በምንም መልኩ ይሁን ስልጣኑን በምርጫ አሳልፎ እንደማይሰጥ፤ በዚህም የስልጣን ወምበርና በኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ ላይ ለመቆየት ደግሞ ማንኛውንም ርምጃ ከመውሰድ እንደማይታቀብ የታወቀ ጉዳይ ነው ብለዋል።

ቀደም ብሎ በተደጋጋሚ እንደተገለጸውና እንደሚታወቀው የግንቦት 7 ንቅናቄ የወያኔ አገዛዝ በፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንገድና በምርጭ ፍጹም ስልጣን እንደማይለቅ መግለጹ እንዲሁም እውነተኛ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ከጎኑ እንዲቆሞ ተደጋጋሚ ጥሪ ማድረጉ አይዘነጋም።

## ወያኔ በ1977ቱ ረሃብ ለትግራይ ተጎጂዎች . . . ከገጽ 1 የዞረ

ይህንኑ ቅሌት በተመለከተ መለስ ዜናዊ የሚሰጠውን ምላሽ ለመዘገብ ተፈልጎ እንደነበር በዘገባው ያካተተው የቢቢሲ ጋዜጠኛ ማርቲን፤ 'አሁን የሚታየው ከፍተኛ ችግር እያሳሰበን ባለበት ጊዜ ከ ከ25 አመት በፊት በ ተፈጸመ ጉዳይ ላይ መልስ የምንሰጥበት ነገር የለም የሚል ምላሽ ከመለስ ዜናዊ ቢሮ እንደተሰጠው አስታውቆአል። ዜናው ለአለም ህዝብ ይፋ ከሆነ በሁዋላ ግን አባዲ ዘሙ የተባለው የወያኔ ባለስልጣን ዜናውን ለማራከስ ከፍተኛ ሙከራ አድርጓል። አይጋ ፎረም የተባለው የወያኔ አፈቀላጤ ድህረገጽ ጅብ ከሄደ ውሻ ጮህ እንዲሉ በቢቢሲው ጋዜጠኛ ላይ የተለመደውን የስድብ ናዳ አውርዶአል።

ወያኔ የትጥቅ ትግል ያካህድ በነበረበት ወቅት በትግራይ ህዝብ ሥም ከአለም አቀፍ በጎ አድራጊ ድርጅቶች የተገኘውን የህይወት አድን እርዳታ ርካሽ ለሆነው ጸረ አገር የፖለቲካ አላማው ማራመጃ እንደተጠቀመበት በዚህም ምክንያት እርዳታውን አግኘተው ቢሆን ኖሮ ከሞት ለመትረፍ ይችሉ የነበሩ ብዙ ሺ ህጻናት፤ አሮጊትና ሽማግሌዎች ህይወታቸው እንደቅጠል እንዲረገፈ የግንቦት 7 ንቅናቄ በዜና ማሰራጫዎቹ ቀድም ብሎ በስፋት የዘገበበት መሆኑ የሚታወስ ነው።

## ወያኔ በመብራት ሃይል አቅርቦት ቀውስ ውስጥ እንደገና መዘፈቁ ተገለጸ

የወያኔው አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ የግልገል ጊቤ ቁጥር 2 የመብራት ሃይል ምንጭ ተመረቀ በተባለበት ጊዜ "ኢትዮጵያዊያን ከዚህ በሁዋላ የሻማ መብራትን የምትጠቀሙት የልደት በዓላችሁን ስታከብሩ ብቻ ነው" በማለት ከተናገረ በሁዋላ ባሉት አስር ቀናት ውስጥ በተፈጠረው ሰው ሰራሽ ከፍተኛ ችግር ምክንያት አገዛዙ ከፍተኛ የሆነ የመብራት ሃይል ቀውስ ውስጥ የገባ መሆኑን ኢንጂኔሪንግ ኒውስ የተባለ ታዋቂና ተዓማኒነት ያለው የመረጃ ድረገጽ አረጋገጠ። የመረጃ ድረገጹ እንደፈረንጆቹ አቆጣር ፌብሯሪ 26 ቀን ባወጣው ጽሁፉ እንደገለጸው በሃገሪቱ ውስጥ ያሉ ከፍተኛ ሃይል ተጠቃሚ የሆኑ ኢንዱስትሪዎችና ካምፓኒዎች የሃይል ፍጆታቸውን በግማሽ እንዲቀንሱ ትዕዛዝ የተሰጣቸው ሲሆን ይህም የሃይል ፍጆታ ቅነሳ ከሁለት ወራት ለማያንስ ጊዜ የሚዘልቅ ነው።

ከዚሁ የሃይል አቅርቦት እጥረት ጋር በተያያዘ ባሁኑ ሰዓት በሃገሪቱ የኤሌክትሪክ ሃይል አገልግሎት ወደነበረበት ፈረቃ እንደገና የተመለሰ መሆኑን በመግለጽ በተለይም በአዲስ አበባ ባብዛኞቹ ክፍለከተሞች በሳምንት እስከ ሶስት ቀናቶች ለሚሆን ጊዜ የመብራት አገልግሎት የሚቋረጥ መሆኑን የአዲስ አበባ የግንቦት ሰባት ዘጋቢያችን የገለጸልን ሲሆን አንዳንድ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በሰጡት ቀልድ አዘል አስተያየት ያሁኑ መብራት መጥፋት ችግር መለስ ዜናዊ ከዚህ በኋላ ሻማን ለልደት በዓላችሁ ብቻ ትጠቀማላችሁ በማለቱና በርካታዉም የአዲስ አበባ ህዝብ የልደት በዓሉን በማክበር ላይ በመሆኑ ሊሆን እንደሚችል መገመታቸውን ገልጾልናል።

የግንቦት ሰባት ድምጽ ሬዲዮ ባለፉት ሁለት ተከታታይ ፕሮግራሞቹ በግልገል ጊቤ በተከዜና በሌሎችም የሃይል ማመንጫ ግንባታ ስራዎች በተቆጣጣሪ መሃንዲስነት ሲያገለግሉ የነበሩትንና ባሁኑ ሰዓት ወያኔ እያከናወነ ያለው የጥፋት ተግባር አስመርሯቸው ለስደት የተዳረጉትን ኢንጂነር ብሩክ ተሾመን በማነጋገር በግንባታ ስራዎቹ ዙሪያ ያሉ ሻጥሮችንና ከፍተኛ ሙስና የሚገልጽ ዝግጂት ማቅረባችን ይታወሳል።

## ወያኔ ለሚቀጥሉት 15 አመታት ያለምንም . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አስተያየት ሰጪዎቹ አክለውም ዲሞክራሲን ማስፋፋት የስራ ዕድልን በመከልከልና ዜጎች የስራ ዕድልንም ለማግኘት በግዴታ የአገዛዙ ወገንተኛ እንዲሆኑ በማድረግ አለመሆኑን ገልጸው ዲሞክራሲን ማስፋፋት ማለት ምሉዕ የሆኑ የዜጎችን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ማክበር፣ ዜጎቹም በፈለጉትና በወሰኑት የፖለቲካ ፓርቲ ተደራጂተው በነጻነት የሃገሪቱን ሁለገብ እድገት እንዲያፋጥኑ ማድረግ ነው በማለት የወያኔን ተራ ውሸት አጋልጣዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት "ወያኔ ከግንቦት 97 ምርጫ ወዲህ ትምህርት የተማረ መስሎን ነበር ሆኖም በተግባር ግን ምንም ነገር አለመማሩን ከሰሞኑ አባባሉ ተረድተናል" ማለታቸውን ዘጋቢያችን የገለጸ ሲሆን፣ የወያኔ አገርን የመምራት አቅምና ቺሎታ በ97 የምርጫ ቅስቀሳ ወቅት በግልጽ መታየቱን በዚያም የክርክር መድረክ የቅንጂት ተፎካካሪዎችን ሩብ ያህል ያመራር ቺሎታ ያላቸው መሪዎች በወያኔ ዘንድ አለመኖራቸውን ህብርተሰቡ ግንዛቤ መውሰዱን ተናግረዋል።

የተቃዋሚ መሪዎች አያይዘውም"አገርን መምራት እቺላለሁ የሚል ፓርቲ የሃገርን ብሄራዊ ጥቅምና ክብር ማስጠበቅ መቻልና ራዕይም ያለው መሆን እንደሚጠበቅበት ነገር ግን የወያኔው አገዛዝ በተቃራኒው ይህንን ለማድረግ ብሄራዊ ራዕይም ሆነ አቅም የሌለው ከመሆኑ በላይ የህዝብም ውክልና የሌለው ነገር ግን ብሄራዊ ጥቅሞችን እንደ ሱዳን ላሉ ሃገራት አሳልፎ በመስጠት የሃገሪቱን ሏአላዊነት ያስደፈረና ህዝቡንም በዘር ከፋፍሎ እያጋጨና እያመሰ የሚገኝ የወንበዴ ቡድን ነው" ብለዋል፡፡

በመጨረሻም የወያኔው አገዛዝ እስካሁን በስልጣን ላይ እንዲቆይ ያደረገው በአመራር ቺሎታውና ባለው ብሄራዊ ራዕይ አለመሆኑን ነገር ግን በዘር ላይ በተመሰረተና በወታደራዊ የደህንነት መዋቅሩ በመታገዝ በጥቅም፤ በዘር ላይ የተመሰረተ ትሥስርና የስልጣን ክፍፍልና አስተሳሰብ በማራመድ ብቻ ነው ሲሉ አጠቃልለዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ወያኔ በተለመደው የክህደት አሰራሩ ለምርጫ 2002 የስነ ምግባር ደንብ የፈረሙ ፓርቲዎች አቋቋምን ያሉትን የጋራ ምክር ቤት በበላይነት ካልመራሁ በማለቱ በወያኔና በሌሎቹ ፓርቲዎች መካከል ከፍተኛ ውዝግብ መፈጠሩን የጋራ ምክር ቤት አባል ሆነናል ያሉትም ተቃዋሚ ፓርቲዎች መደናገጣቸውን ገልጸዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661